የክትባት መረጃ መግለጫ:

# Meningococcal ACWY ክትባት:
## ማወቅ የሚገባዎት

Many Vaccine Information Statements are available in Spanish and other languages. See www.immunize.org/vis

Hojas de información sobre vacunas están disponibles en español y en muchos otros idiomas. Visite www.immunize.org/vis

## 1 መከተብ ለምን አስፈለገ?

**Meningococcal (ሜኒንጆኮካል)** በሽታ ከባድ የሆነ በሽታ ሲሆን *Neisseria meningitidis* (ኒዬየሴሪያ ሜኒንጃይተስ) በሚባል ባክቴሪያ አማካይነት የሚፈጠር ነው። ለሜኒንጃይተስ (የአእምሮ እና የህብለ ሰረሰር መስመር ኢንፌክሽን) እና ለደም ኢንፌክሽን ሊዳርግ ይችላል። Meningococcal (ሜኒንጆኮካል) በሽታ አብዛኛውን ጊዜ ያለምንም ማስጠንቀቂያ የሚፈጠር ሲሆን ጤናማ በሆኑ ሰዎች ላይ ይከሰታል።

Meningococcal በሽታ ከሰው ወደ ሰው ቅርብ በሆነ ንክኪ (በማሳል ወይም በመሳሳም) ወይም በረጅም ንክኪ፣ በተለይ አንድ ቤት ውስጥ በሚኖሩ ሰዎች መሃከል ሊስፋፋ ይችላል።

ቢያንስ 12 አይነት *N. meningitidis*, ያሉ ሲሆን “serogroups” በመባል ይጠራሉ። Serogroups A፣ B፣ C፣ W፣ እና Y አብዛኛውን የ meningococcal ህመም የሚፈጥሩ ናቸው።

ሁሉም ሰው የ meningococcal በሽታ ሊያዝ ይችላል ነገር ግን አንዳንድ ሰዎች ከሌላ በተለየ የበለጠ ስጋት:

- ከአንድ ዓመት በላይ የሆኑ ህጻናት
- ከ 16 እስከ 23 ዓመት ውስጥ ያሉ ጎረምሶችና ወጣቶች
- የሰውነት የመከላከል አቅምን የሚጎዳ በሽታ ታማሚዎች
- ከ *N. meningitidis* ጋር ተለይተው የሚሰሩ ማይክሮ ባዮሎጂስቶች
- በወረርሽኝ ጊዜ ስጋት ውስጥ ያሉ ሰዎች

በሚታከምበትም ጊዜ፣ በሽታ ከ 100 ሰዎች ውስጥ ከ 10 እስከ 15 የሚሆኑትን ይገድላል። ከተረፉት 100 ውስጥ ሰዎች ከ10 እስከ 20 ሰዎች እንደ የመስማት ችግር፣ የአእምሮ ጉዳት፣ የኩላሊት ጉዳት፣ እግር መቆረጥ፣ የነርቨስ ሲስተም ችግሮች ወይም ከቆዳ ችግር የተነሳ ጠባሳ ችግሮች ያጋጥማቸዋል።

**Meningococcal ACWY ክትባት** meningococcal በሽታ ፈጣሪ የሆኑትን serogroups A, C, W, እና Y ን ይከላከላል። የተለየ የ meningococcal ክትባት ከ serogroup B የሚከላከል ክትባት ነው።

## 2 Meningococcal ACWY ክትባት

Meningococcal conjugate ክትባት (**MenACWY**) ምግብ እና መድሀኒት አስተዳደር (FDA) ፈቃድ ያለው ሲሆን ከ serogroups A, C, W, እና Y ይከላከላል።

ከ 11 እስከ 18 ዓመት ዕድሜ ላይ ለሚገኙ ታዳጊዎች ሁለት የ MenACWY ዶሶች በተደጋጋሚ ይመከራሉ: የመጀመሪያው ዶስ ለ 11 ወይም ለ 12 ዓመት፣ ለ 16 ዓመት ደግሞ የጨመረ ዶስ። አንዳንድ ታዳጊዎች፣ HIV ያለባቸውንም ጨምሮ፣ ተጨማሪ ዶስ ማግኘት አለባቸው። ለበለጠ መረጃ የህክምና እንክብካቤ ሰጪዎን ያማክሩ።

ለታዳጊዎች ተደጋጋሚ ክትባት ከመስጠት በተጨማሪ፣ MenACWY ክትባት ለአንዳንድ ሰዎች መስጠት ይመከራል።

- በ serogroup A፣ C፣ W፣ ወይም Y meningococcal በሽታ ወረርሽኝ ጊዜ ለአደጋ የሚጋለጡ ሰዎች
- በ HIV (ኤችአይቪ) የተያዙ ሰዎች
- ማንኛውም ቆሽቱ የተጎዳ ወይም የወጣ እንዲሁም የ sickle ሴል በሽታ ያለበት ሰው።
- “Persistent complement component deficiency” በሚባል በጣም አልፎ አልፎ በሚከሰት የበሽታ መከላከል አቅም መዳከም ያለበት ሰው
- ማንኛውም eculizumab (ወይም Soliris®) የሚባል መድሀኒት የሚወስድ ሰው
- ከ *N. meningitidis* ጋር ተለይተው የሚሰሩ ማይክሮ ባዮሎጂስቶች
- ለምሳሌ እንደ አፍሪካ ውስጥ ያሉ meningococcal በሽታዎች በብዛት ወደሚገኙባቸው ቦታዎች መጓዝ፣ መኖር
- በዶርም ውስጥ የሚኖሩ አዲስ የኮሌጅ ተማሪዎች
- የአሜሪካ ውትድርና ተቀጣሪዎች

አንዳንድ ሰዎች ከፍ ያለ መከላከያ ዶዝ ያስፈልጋቸዋል። ምን ያህል እና በየስንት ጊዜ እንደሚወሰድ እንዲሁም ቡስተር ዶሶችን በተመለከተ የጤና እንክብካቤ ሰጪዎን ይጠይቁ።



U.S. Department of Health and Human Services
Centers for Disease Control and Prevention

## 3 አንዳንድ ሰዎች ይህንን ክትባት መውሰድ የለባቸውም

ክትባቱን ለሚስጥዎ ሰዎ ምንም አይነት ህይወትን አደጋ ላይ ሊጥል የሚችል አለርጂክ ያለብዎ ከሆነ ያሳውቁ። ከዚህ በፊት ከወሰዱት ከ meningococcal ACWY ክትባት ዶስ የተነሳ ህይወትን አደጋ ላይ የሚጥል አለርጂ ከተነሳብዎ ወይም ከዚህ ክትባት ጋር በተያያዘ ከባድ አለርጂ አጋጥምዎ የሚያውቅ ከሆነ፣ ይህንን ክትባት አይውሰዱ። ስለ ክትባቱ ይዘቶች ክትባት ሰጪዎ ሊነግርዎት ይችላል።

እርጉዝ ለሆነች ወይም ለምታጠባ ሴት ስለዚህ ክትባት ብዙ የሚታወቅ ስጋት የለም። ነገር ግን እርግዝና እና ማጥባት የ MenACWY ክትባትን ላለመውሰድ ምክንያት አይደለም። እርጉዝ ወይም የምታጠባ ሴት ከፍ ያለ በ meningococcal የመያዝ እድል ያላት እንደሆነ ክትባቱን መውሰድ አለባት።

ከባድ ያልሆነ ህመም ማለትም እንደ ጉንፋን ያለ ህመም ካለብዎ ዛሬውኑ ክትባቱን ሊያገኙ ይችላሉ። ከበድ ያለ ወይም በጣም ህመም ላይ ከሆኑ፣ እስኪሻልዎ ድረስ ይጠብቁ። ሀኪምዎ ሊያማክርዎ ይችላል።

## 4 የክትባተ ምላሽ ስጋት

ክትባትን ጨምሮ በሁሉም መድሀኒቶች የጎንዮሽ ጉዳት የመፈጠር እድል አለ። እነዚህ መለስተኛ ሲሆኑ በትንሽ ቀናት ውስጥ በራሳቸው የሚጠፉ ናቸው፤ ነገር ግን ከባድ ህመም ሊፈጠር ይችላል።

Meningococcal ACWY ክትባትን ከሚወስዱ ግማሽ ሰዎች ከክትባት በኋላ መለስተኛ ህመም የተወጋበት ቦታ ላይ መቅላት መይም መቁሰል ያጋጥማቸዋል። እነዚህ ችግሮች የሚጠሩ ከሆነ፣ ከ 1 እስከ 2 ቀናት ድረስ ይቆያሉ።

ክትባቱን ከሚወስዱ ሰዎች ውስጥ ዝቅተኛ ፐርሰንት ያላቸው ሰዎች የጡንቻ እና መገጣጠሚያ ህመም ይሰማቸዋል።

**የትኛውንም ክትባት ከወሰዱ በኋላ የሚያጋጥሙ ችግሮች:**

- ከህክምና በኋላ፣ ክትባትን ጨምሮ ሰዎች አንዳንድ ጊዜ ራሳቸውን ይስታሉ። ለ15 ደቂቃ መቀመጥ ወይም መተኛት ራስን መሳት እንዲሁም በመውደቅ የሚመጣውን ጉዳት ይከላከላል።የሚያዞርዎ ከሆነ ወይም የእይታ ችግር ካለ ለሀኪምዎ ያሳውቁ።
- ንዳንድ ሰዎች ትከሻ ላይ ከበድ ያለ ህመም ሲሰማቸው የተወጉበት አጃቸውን ማንቀሳቀስ ያስቸግራቸዋል። ይህ አልፎ አልፎ የሚከሰት ነው።
- የትኛውም መድኃኒት ከበድ ያለ የአለርጂክ ሊያስነሳ ይችላል። ከክትባት የሚመጡ አለርጂኮች በጣም አልፎ አልፎ የሚከሰቱ ሲሆኑ 1 ከ 1 ሚሊዮን ይገመታል እናም ከክትባት ጊዜ በትንሽ ሰዓት ውስጥ ይጀምራሉ።

ልክ እንደ ሌላው መድኃኒት፣ ክትባት በጣም ከባድ ጉዳት ወይም ሞት የሚያስከስትልበት በጣም ጠባብ እድል አለ።

የክትባቶች ደህንነት ሁልጊዜ በቅርብ ክትትል ውሰጥ ነው። ለበለጠ መረጃ ይህን ይጎብኙ፡ **www.cdc.gov/vaccinesafety/**

## 5 አደገኛ የሆነ የአለርጂ ምልክት ቢኖርስ?

**ማየት ያለብኝ ምንድነው?**

- ስጋት የሆነብዎትን ነገር እንደ ከባድ የአለርጂክ ምልክት፣ ከፍተኛ ትኩሳት ወይም ያልተለመዱ ባህርያትን ይመልከቱ።

  ከፍተኛ የሆነ አለርጂክ እንደ ሀይቭ፣ የፊት እና ጉሮሮ ማበጥ፣ የመተንፈስ ችግር፣ ከፍተኛ የልብ ምት፣ ማዞር እና ድካም የሚያካትት ሲሆን — ክትባቱን በወሰዱ በጥቂት ደቂቃዎች ወይም ሰአቶች ውስጥ ነው።

**ምን ማድረግ አለብኝ?**

- ከባድ የሆነ የአለርጂክ ምልክት ወይም ሊቆይ የማይችል አስቸኳይ ከመሰለዎት 9-1-1 በመደወል አቅራቢያ ወዳለው ሆስፒታል ይሂዱ።ካለበለዚያ ሀኪምዎ ጋር ይደውሉ።

  ከዚያ በኋላ የአለርጂው ምልክት ለ "Vaccine Adverse Event Reporting System" (VAERS) ሪፖርት መደረግ አለበት። ሃኪምዎ ይህንን ፋይል ሪፖርት ማድረግ አለበት ወይም እርስዎ ራስዎ የ VAERS ድረ ገጽን በ **www.vaers.hhs.gov**፣ በመጠቀም ወይም በ **1-800-822-7967** መደወል

ይችላሉ። *VAERS* የህክምና ምክር አይሰጥም።

## 6 ብሄራዊ የክትባት ጉዳት ካሳ ፕሮግራም

ብሄራዊ የክትባት ጉዳት ካሳ ፕሮግራም (VICP) የፌደራል ፕሮግራም ሲሆን በአንዳንድ ክትባቶች ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸውን ሰዎች የሚካስ ድርጅት ነው።

በአንድ ክትባት ምክንያት ጉዳት ደርሶብናል ብለው የሚያስቡ ሰዎች ስለ ፕሮራሙ መማር እና እንዴት የይገባኛል ፎርም መሙላት እንዳለባቸው መማር ይችላሉ። 1-800-338-2382 ላይ በመደወል ወይም VICP ድረገጽን በመጎብኘት **www.hrsa.gov/vaccinecompensation**. የካሳ ይግባኝ ጥያቄ የማቅረቢያ የጊዜ ገደብ አለ።

## 7 እንዴት የበለጠ ማወቅ እችላለሁ?

- የጤና እንክብካቤ ሰጪዎን ይጠይቁ። እርሱ ወይም እርሷ የክትባቱን ማብራሪያ ወረቀት ወይም ሌላ የመረጃ ምንጭን መጠቆም ይችላል/ትችላለች።
- የአካባቢያዎ ወይም የከተማው የጤና ክፍል ጋር ይደውሉ።
- Centers for Disease Control and Prevention (CDC) ን ያግኙ:

  - ለ **1-800-232-4636** (**1-800-CDC-INFO**) ይደውሉ - ወይም

  - **www.cdc.gov/vaccines** ድረገጽን ይጎብኙ።

Vaccine Information Statement (Interim)
Meningococcal ACWY Vaccines
Amharic

Office use only

08/24/2018 | 42 U.S.C. § 300aa-26

Translation provided by the Minnesota Department of Health